የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮ ዓ.ም
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 26
ADDIS ABABA March 23th, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፭/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ……………..………...ገጽ ፲፪ሺ፫፻፴፱

**Content**

Proclamation No. 1185 /2020

Hate Speech and Disinformation Prevention and Suppression Proclamation ……..……………. Page 12339

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፭/፪ሺ፲፪

## የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

ሆን ተብሎ የሚሰራጩ የጥላቻና ሐሰተኛ ንግግሮችን በሕግ መከልከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማህበራዊ ስምረት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሃገራዊ አንድነት፣ ለሰብአዊ ክብር፣ ለብዝሃነትና ለእኩልነት ጠንቅ መሆኑን በመገንዘብ፤

መሰረታዊ መብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ የተደነገጉ፣ በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን አላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ፣ ተመጣጣኝና በጠባቡ የተበጁ መሆን እንዳለባቸው በመገንዘብ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1185 /2020

## HATE SPEECH AND DISINFORMATION PREVENTION AND SUPPRESSION PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to prevent and suppress by law the deliberate dissemination of hate speech and disinformation,

**COGNIZANT,** of the threat hate speech and disinformation pose to social harmony, political stability, national unity, human dignity, diversity and equality,

**RECOGNIZING,** that limitations on fundamental rights should be proportionate, narrowly tailored and prescribed by law in pursuit of aims that are legitimate in a democratic society,

**NOW THEREFORE,** In accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፭/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ትርጉም</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ንግግር"** ማለት በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽ እና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች መልእክትን የማሰራጨት ተግባር ነዉ፤

፪/ **"የጥላቻ ንግግር"** ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠረ፣ ብሔርን፡ብሔረሰብንና ህዝብን፣ ሃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር ነው፤

፫/ **"ሐሰተኛ መረጃ"** መረጃው ሐሰት የሆነና የመረጃውን ሐሰተኝነት በሚያውቅ፣ ወይም መረጃውን የሚያሰራጨው ሰው ካለበት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር የመረጃውን እውነተኝነት ለማጣራት በቂ ጥረት ሳያደርግ የሚሰራጭ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት፣ ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ ዕድሉ ከፍ ያለ ንግግር ነው፤

፬/ **"ብሮድካስት ማድረግ"** ማለት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ሥርጭት ማድረግ ነዉ፤

፭/ **"መድሎ"** ማለት ብሔርን ብሔር ብሔረሰብን ህዝብን ሃይማኖትን ዘርን ፆታን አካል ጉዳተኝነትን ወይም ሌሎች በህግ የተጠበቁ ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ የሚፈጸም የማግለል ተግባር ነው፤

፮/ **"ጥቃት"** ማለት በግለሰብ ወይም በቡድን አባላት ንብረት፤አካል ወይም ሕይወት ላይ የሚፈጸም ጉዳት ነው፤



**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Hate Speech and Disinformation Prevention and Suppression Proclamation No.1185 /2020."

**2. <u>Definition</u>**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ **"Speech"** means the act of disseminating of information verbally, textually, graphically or by other means;

2/ **"Hate speech"** means speech that deliberately promotes hatred, discrimination or attack against a person or an discernable group of identity , based on ethnicity, religion, race, gender or disability;

3/ **"Disinformation"** means speech that is false, is disseminated by a person who knew or should reasonably have known the falsity of the information and is highly likely to cause a public disturbance, riot, violence or conflict;

4/ **"Broadcasting"** means radio or television transmission;

5/ **"Discrimination"** means any act of denying including legally accepted and attack against a person or a group based on ethnicity, religion, gender or disability;

6/ **"Violence"** means any injury of property, body or life against on an individual or a group of people;

፯/ “**ማሰራጨት**” ማለት ንግግርን በማናቸውም መንገዶች ለብዙ ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ሲሆን በማህበራዊ ሚዲያ ላይክ ማድረግና ታግ ማድረግን አያካትትም ፤

፰/ "**ማህበራዊ ሚዲያ**" ማለት ሰዎች መልዕክት ለመለዋወጥ ፤ ትስስር ለማዳበር፤ ሀሳብ ለመጋራት የሚጠቀሙበት በኢንተርኔት አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት፣ ወይም ማህበራዊ መስተጋብር የሚስተናገድበት መንገድ ነዉ፤

፱/ “**የህትመት ሚዲያ**” ማለት ለህዝብ ስርጭት የተዘጋጀ ማንኛውም የህትመት ወጤት ነው፤

፲/ “**ማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት**” ማለት የማህበራዊ ሚዲያ አውታርን ወይም መድረክን ለተጠቃሚዎች የሚያደርስ ድርጅት ነው፤

፲፩/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸ ድንጋጌ ለሴት ጾታ ያገለግላል፡፡

**፫. <u>አላማ</u>**

የአዋጁ አላማዎች፡-

፩/ ሰዎች ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ ግጭት ወይም ሁከትን የሚቀሰቅስ ወይም ብሔርን፤ ሃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰብ ወይም በተለየ ቡድን ላይ ጥላቻ ወይም መድልዎ የሚያስፋፋ ንግግር ከማድረግ እንዲቆጠቡ ማድረግ፤

፪/ መቻቻልን፣ የዜጎች ውይይትና ምክክርን፣ መከባበርና መግባባትን ማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማጎልበት፤

፫/ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃና መረጃዎችን ስርጭት መበራከትን ለመቆጣጠርና ለመግታት ነው።

7/ “ **Dissemination**” means spread or share a speech on any means for many person, but it does not include like or tag on social media;

8/ **“Social Media”** means any social interactive method that facilitate the creation and sharing of information for more than one person at one time and Social networking through the internet;

9/ “**Print Media**” means any printed material prepared for public dissemination or distribution;

10/ **“Social Media Servicing Enterprises”** means an enterprise which delivers a social media network or platform to the users;

11/ **“Person”** means a natural person or juridical person;

12/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Objectives</u>**

The objectives of the Proclamation are to:-

1/ Ensure that in their exercise of freedom of expression, individuals will not engage in speech that incites violence, is likely to cause public disturbance or promotes hatred and discrimination against a person or an identifiable group or community based on ethnicity, religion, race, gender or disability;

2/ Promote tolerance, civil discourse and dialogue, mutual respect and understanding and strengthening democratic governance;

3/ Control and suppress the dissemination and proliferation of hate speech, disinformation and other related false and misleading information.

**፬. የጥላቻ ንግግር ስለመከልከሉ**

ማንኛውም ሰው የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

**፭. የሐሰት መረጃን ማሰራጨት ስለመከልከሉ**

ማንኛውም ሰው የሐሰት መረጃን በአደባባይ ስብሰባዎች በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ ተግባር ነው፡፡

**፮. ልዩ ሁኔታ**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ እና ፭ እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር ወይም እንደ ሐሰት መረጃ ተወስዶ ማሰራጨት የማይከለከለው፡-

ሀ) የትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር አካል እንደሆነ፤

ለ) የዜና ዘገባ፤ ትንታኔ ወይም የፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ፤

ሐ) የኪነጥበበ ፣ ትወና ወይም መሰል የስነጥበበ ውጤት ከሆነ፣

መ) የሃይማኖታዊ አስተምህሮት አካል እንደሆነ ነው።

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ንግግር እንደ ሐሰተኛ መረጃ ተወስዶ የማይከለከለው ንግግሩን ያሰራጨው ወይም ያደረገው ሰው የመረጃውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ በሱ ሁኔታ ካለ ሰው የሚጠበቀውን ምክንያታዊ ጥረት ያደረገ እንደሆነ ወይም ንግግሩ የጥሬ ሐቅ ዘገባ ወይም ዜና ከመሆን ይልቅ ወደ ፖለቲካ አስተያየትና ትችትነት ያጋደለ ከሆነ ነው።



**4. Prohibition of Hate Speech**

Any person disseminating hate speech by means of broadcasting, print or social media using text, image, audio or video is prohibited.

**5. Prohibition of Disseminating Disinformation**

Disseminating of any disinformation on public meeting by means of broadcasting, print or social media using text, image, audio or video is a prohibited act.

**6. Exemptions**

1/ Notwithstanding Articles 4 and 5 of this Proclamation, a speech will not be considered hate speech or disinformation and its dissemination is not prohibited if it is part of;

a) An academic study or scientific inquiry ,

b) A news report, analysis or political critique,

c) Artistic creativity, performance or other form of expression,

d) Religious teaching.

2/ Notwithstanding to Article 5 of this Proclamation, a speech will not be considered as disinformation and prohibited if a reasonable effort has been made under the circumstances by the person making the speech to ensure the veracity of the speech or if the speech is more inclined to political commentary and critique instead of being a factual or news report.

## ፯. የወንጀል ተጠያቂነት

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ መሰረት የተከለከለውን የጥላቻ ንግግር ያደረገ እንደሆነ እስከ ሁለት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል።

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ መሰረት ክልከላ የተደረገበትን ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እስከ አንድ አመት በሚደርስ በቀላል እስራት ወይም ከብር ፶ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬/ የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ከሆነ ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ቅጣቱ እስከ ሶስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

፭/ ሐሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ከሁለት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል።

፮/ በጥላቻ ንግግር ወይም በሐሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈጸም ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ እና ጥፋተኛውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን ይችላል።

## 7. Criminal Liability

1/ Any person who commits acts proscribed under Article 4 shall be punished with simple imprisonment not exceeding two years or a fine not exceeding 100,000 birr.

2/ If an attack against a person or a group has been committed as a result of a hate speech, the punishment shall be simple imprisonment not exceeding from one year up to five years.

3/ Any person who commits acts proscribed under Article 5 shall be punished with simple imprisonment not exceeding one year or a fine not exceeding 50,000 birr.

4/ If the offense of hate speech or disinformation offense has been committed through a social media account having more than 5,000 followers or through a broadcast service or print media, the person responsible for the act shall be punished with simple imprisonment not exceeding three years or a fine not exceeding 100,000 birr.

5/ If violence or public disturbance occurs due to the dissemination of disinformation, the punishment shall be rigorous imprisonment from two year up to five years.

6/ If no violence or public disturbance has resulted due to the commission of the offense of hate speech or disinformation and if a court of law is convinced that the correction of the convict will be better served through alternatives other than fine or imprisonment, the court could sentence the convict to render mandatory community service.

## ፰. የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎች ኃላፊነት

፩/ ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመግታት ጥረት ማድረግ አለበት።

፪/ ድርጅት የጥላቻ ንግግርን ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን የተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ ይህን መሰል መልዕክቶችን ወይም ንግግሮችን ከአግልግሎት አውታሩ ሊያስወግድ ይገባል።

፫/ ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተንደነገገውን ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለው አሰራርና ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል።

፬/ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ የተቀመጠውን ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን እየተከታተለ ለህዝብ ይፋ የሚሆን ሪፖርት ያዘጋጃል።

፭/ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የሐሰት መረጃ ስርጭትና ጉዳትን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

፮/ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

፯/ የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎች ኃላፊነትን ዝርዝር የሚደነግግ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊወጣ ይችላል።

## 8. Duties of Institutions and Service Providers

1/ Any enterprise that provides social media service should endeavor to suppress and prevent the dissemination of disinformation and hate speech through its platform.

2/ Social media service providers should act within twenty four hours to remove or take out of circulation disinformation or hate speech upon receiving notifications about such communication or post.

3/ Social media enterprises should have policies and procedures to discharge their duty under sub article (1) and (2) of this Article.

4/ The Ethiopian Broadcast Authority shall prepare a report which is notify to the public on social media enterprises whether they discharge their duty properly under sub this article.

5/ The Ethiopian Broadcast Authority shall conduct public awareness and media literacy campaigns to combat disinformation.

6/ The Ethiopian Human Rights Commission shall conduct public awareness campaigns to combat hate speech.

7/ The Council of Ministers may issue a Regulation to provide for the detail responsibilities of service providers and relevant Governmental Institutions.

**፱. <u>ስለተሻሩ ህጎች</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ ፬፻፹፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

**፲. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**9. <u>Repealed Laws</u>**

Article 486 of the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby repealed.

**10. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 23th Day of March, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**